አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ ጥር ፳ ፪ሺህ፪ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2ND YEAR NO.30
ADDIS ABABA JANUARY 28,2010


**ማውጫ**


በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲን አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፫፻፳፰


**CONTENTS**


THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT MICRO AND SMALL SCALE ENTERPRISE DEVELOPMENT AGENCY ORGANIZATIONAL STRUCTURE AND WORK PROCEDURE REGULATION 328


## ደንብ ቁጥር ፴/፪ሺ፪

## የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲን አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ ድህነትንና ስራ አጥነትን ለመቅረፍ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ማቋቋምና ማስፋፋት ከአስተዳደሩ ቁልፍ ተግባራት አንዱ በመሆኑ፤

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዝ ልማት ለከተማ ድህነት ቅነሳ እንዲሁም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት ሊተካ የማይችል ሚና ያለው መሆኑ ስለታመነ፤

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማትን ውጤታማ ለማድረግ የበርካታ ሴክተር መስሪያ ቤቶችን ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ በዘርፉ የተሰማሩ አንቀሳቃሾችን በማስተባበር በስራ ፈጠራ፣ በገበያ ትስስር፣ በመስሪያ ቦታ አቅርቦት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በመሳሰሉት ድጋፎች ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ከመሰረቱ በመቅረፍ ዘርፉን ለተሻለ ውጤት ማብቃት በማስፈለጉ፤

## REGULATION NO.30/2010

## A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ORGANIZATIONAL STRUCTURE AND WORK PROCEDURE OF MICRO AND SMALL SCALE ENTERPRISE DEVELOPMENT AGENCY

**WHEREAS,** establishing and extending micro and small scale enterprises and thereby alleviating poverty and unemployment in Addis Ababa City is one of the key functions of the City Government;

**WHEREAS,** it is believed that micro and small scale enterprise development has irreplaceable role in reduction of urban poverty and even bringing about rapid and sustainable development;

**WHEREAS,** it is found necessary to make the sector successful by alleviating the problems, by coordinating operators involved in the sector, regarding job creation, market bond, providing place for work, technology transfer and other similar supports since the success of micro and small scale enterprise development demands participation of several sector offices;


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ኤጀንሲዉ የተቋቋመለትን ዓላማ እንዲሁም ተግባራቱን በአግባቡ እንዲወጣ አደረጃጀቱንና የአሠራር ሥርዓቱን ለመወሰን ደንብ ማዉጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩/ረ/ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺህ፩ አንቀጽ ፸፱ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲን አደረጃጀትና አሰራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፴/፪ሺህ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"የከተማ" አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ቦርድ"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ መሠረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲን በበላይነት የሚመራ አካል ነው፤

፬. **"ቢሮ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤

፭. **"ኤጀንሲ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አካላትን እንደገና ማቋቋሚ አዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺህ፩ አንቀፅ ፲፬ መሰረት የተቋቋመ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ነው፤

፮. **"ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ"** ማለት በማናቸውም የማምረት፣ የመነገድ ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባር ላይ የተሰማራና የተከፈለ ካፒታል መጠኑ እስከ ብር ፳ሺ./ሃያ ሺህ ብር/ የሆነ ኢንተርፕራይዝ

**WHEREAS**, it is found necessary to issue regulation to provide for the organizational structure and work procedure to enable the Agency properly discharge the objectives and functions;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 23/1/f/ of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No.361/2003 and Article 79 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Services Organs Re-establishment Proclamation No.15/2009 Cabinet of the City Government hereby issued this Regulation.

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "A Regulation to provide for the Organizational Structure and Work Procedure of Micro and Small Scale Enterprise Development Agency of the Addis Ababa City Government Regulation No.30/2010".

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in these regulations:

1. **"City"** means the Addis Ababa City;
2. **"City Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Board"** means a body established in accordance with Article 8 of this regulation to direct superiorly the Micro and Small Scale Enterprise Development Agency of the Addis Ababa City Government;
4. **"Bureau"** means the Bureau of Trade and Industry Development of the Addis Ababa City Government;
5. **"Agency"** means the Micro and Small Scale Enterprise Development Agency established in accordance with Article 14 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No. 15/2009;
6. **"Micro Enterprise"** means an enterprise involved in the activity of production, trade, or service rendering and has paid up capital of 20,000

ሲሆን፤ የከፍተኛ ቴክኖሎጂ ባለቤት የሆኑ ድርጅቶችን በማማከር አገልግሎት ላይ የተሰማሩትን አያካትትም፤

፯. **"አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት በማናቸውም የማምረት፣ የመነገድ ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባር ላይ የተሰማራና የተከፈለ ካፒታል መጠኑ ከብር ፳ሺ.ህ /ሃያ ሺ.ህ ብር/ እስከ ብር ፭፻ሺ. /አምስት መቶ ሺ.ህ ብር/ ድረስ ሲሆን፤ የከፍተኛ ቴክኖሎጂ ባለቤት የሆኑ ድርጅቶችን በማማከር አገልግሎት ላይ የተሰማሩትን አያካትትም፤

፰. **"ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ሰዎች በማህበር ወይም በሌላ በህግ በተፈቀደ አደረጃጀት ተደራጅተውና ህጋዊ ሰውነት አግኝተው በመረጡት የጥቃቅንና አነስተኛ ሥራ ማለትም በማምረት፣ በመነገድ ወይም አገልግሎት በመስጠት ላይ የተሰማራ ተቋም ነው፤

፱. **"አንቀሳቃሽ"** ማለት በቡድን በመደራጀት ወይም በግል በመሆን በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራ ይዝ በባለቤትነት በመሥራት የገቢ እና የሥራ ዕድል የተፈጠረለት ቡድን ወይም ግለሰብ ነው፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርራይዝ ልማት ኤጀንሲ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ዓላማ፣ አደረጃጀት እና የዳይሬክተሮች አሿሿም

## ፬. የኤጀንሲው ዓላማዎች

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. በአዲስ አበባ የሚታየውን የሥራ አጥነት ችግር በተደራጀ መንገድ መቅረፍ፤

፪. አንቀሳቃሾች በዋነኛነት በሀገር ውስጥ በሚገኝ ጥሬ ሀብት ላይ ተመስርተው ለራሳቸው የገቢ ምንጭ በማግኘት ለከተማው ብሎም ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል፤



/Twenty Thousand Birr/; however, it does not include enterprises involved in providing consultancy service to organizations owning large scale technology;

7. **"Small enterprise"** means an enterprise involved in the activity of production, trade or service rendering and has paid up capital of 20,000 - 500,000 / Twenty Thousand to Five Hundred Thousand/; however, it does not include enterprises involved in providing consultancy service to organizations owning large scale technology;

8. **"Enterprise"** means an institution whereby individuals, organized in association or other lawful form and acquire legal personality, involve in one of the activities of micro and small scale of production, trade or service rendering;

9. **"Operator"** means a group or individual that has acquired income and job opportunity in group or individually by working with ownership title in micro and small scale enterprise.

## 3. Scope of Application

These regulations shall be applicable on the Addis Ababa City Government Micro and Small Scale Enterprise Development Agency.

## PART TWO
## OBJECTIVE, ORGANIZATIONAL STRUCTURE AND APPOINTMENT OF DIRECTORS

## 4. Objectives of the Agency

The agency shall have the following objectives:

1. To alleviate in an integrated manner the problem of unemployment in Addis Ababa City;
2. To enable operators, by getting source of income for themselves basically being dependent upon domestically available raw resources, contribute their respective role in the economic development of the City as well as the Country as a whole;

፫. ስራ ፈላጊዎች ባላቸው መሰረታዊ እውቀት የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ መሰማራት እንዲችሉ የመስሪያ ቦታ በማዘጋጀት፣ በጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ በስልጠና፣ በብድርና ቁጠባ በገበያ ትስስርና በመሳሰሉት በመደገፍ ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ደግሞ ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዝ የሚደረገውን ሽግግር ማፋጠን፤

፬. በአዲስ አበባ ከተማ የሚታየውን የድህነትና የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ በሚካሄደው እንቅስቃሴ በተለይ በኮንስትራክሽን፣ በብረታ ብረትና እንጨት፣ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ በምግብ ዝግጅት፣ በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት፣ በከተማ ግብርና፣ በጥርብ ድንጋይ፣ በፓርኪንግ እንዲሁም በሌሎች ወደፊት በጥናት በሚለዩ እድገት ተኮር የስራ መስኮች የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል ግልፅና ወጥነት ያለው የድጋፍ ፓኬጆችን ማዘጋጀት፣ በየጊዜው ከሚያጋጥሙ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ማሻሻልና በኃላፊነት ስሜት መምራትና ማስፈጸም፤

፭. የተጀመረው ልማት ቀጣይና ተከታታይ እንዲሆን የሥራ ፍቅር በአንቀሳቃሾች ዘንድ እንዲጐለብትና የውድድር ስሜት እንዲሰፍን ማድረግ፤

፮. በከተማው የሚገኙ ነባርና አዳዲስ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚመረቁ ወጣቶች የቴክኖሎጂ ሽግግርና የውጭ ገበያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የምርት ጥራትና መጠን በማሻሻል የውጭ ምንዛሪ እንዲገኝ በተለይ ወደ ውጭ ከሚልኩ ድርጅቶች ጋር በማገናኘት የውጭ ገበያ ዕድል እንዲሰፋ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

3. To intensify the process of transfer from micro to small scale, from small scale to medium and large scale enterprises by supporting in the provision of production sites, supply of raw materials, training, credit and saving, market ties and the like so that the job seekers will be able to involve in income generating activities utilizing their basic skill;

4. To prepare transparent and uniform support packages that enable exhaustive utilization of job opportunities created in the effort to alleviate the problem of poverty and unemployment in Addis Ababa City particularly in the area of construction, metallurgy and wood works, textiles and garment, food preparation, municipality service, urban agriculture, cobble stone, parking and even other development oriented fields of activity to be identified in the future through research; to direct with sense of responsibility and cause implementation of such packages revising and in accordance with the changing circumstances;

5. To initiate the operators develop job affection and bring about sense of competition with the view to make the ongoing development sustainable and continuous;

6. To facilitate the conditions for the promotion of foreign market opportunity especially by collaborating with exporting organizations, with the view to cause the existing or new micro and small scale enterprises and even the youth graduating from technical and vocational institutions benefit from transfer of technology and foreign market and thereby improving the quality and quantity of production to acquire hard currency.

## ፭. አደረጃጀትና አሿሿም

፩. ኤጀንሲው የሚከተሉት አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡-

ሀ. አንድ ዋና ዳይሬክተር፣

ለ. ሁለት ምክትል ዳይሬክተሮች፣

ሐ. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የስራ ሂደት መሪዎች እና ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

፪. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተሮች በከተማው ከንቲባ ይሾማሉ፡፡

## ፮. የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

፩. ዋና ዳሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ. በአዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፩ የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ. በመንግስት ሰራተኞች አስተዳደርና በዚህ ደንብ መሰረት የኤጀንሲውን ሰራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ሐ. የኤጀንሲውን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

መ. ለኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀትና ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ. ኤጀንሲው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፣

ረ. የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በወቅቱ ለከንቲባው ያቀርባል፡፡

፫. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተሮች ወይም ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## 5. Organizational Structure and Appointment

1. The Agency shall have the following organizational structure፡
   a. One Chief director;
   b. Two Deputy Directors;
   c. Process owners and necessary staffs.
2. The chief director and deputy directors of the Agency shall be appointed by the Mayor of the City.

## 6. Power and Function of the Chief Director

1. The chief director, being the chief executive of the Agency, shall manage and direct its functions.
2. Without prejudice to the provisions of sub-article 1 of this article the chief director shall:
   a. implement power and functions of the Agency specified under Proclamation No 15/2009;
   b. employ, administer and dismiss employee of the Agency in accordance with the civil service law and this regulation;
   c. prepare strategic plan, annual working program and budget of the Agency and implement same upon approval;
   d. discharge finance in accordance with the allocated budget and annual working program of the Agency;
   e. represent the Agency in relationships with third parties;
   f. Submit timely performance report to the Mayor.
3. The Chief Director may delegate his power and functions to the deputy directors or other officials and workers of the Agency, to the extent necessary to facilitate the functions of the Agency.

፬.ከከንቲባዉ ወይም ከቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፯.የምክትል ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

፩. ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጥ መመሪያ መሠረት፡-

ሀ. የኤጀንሲውን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤

ለ. የዘርፋቸውን ዕቅድ በማዘጋጀትና በማፀደቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

ሐ. በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎች ያከናውናሉ፡፡

፪. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ዉክልና የተሰጠዉ ምክትል ዳይሬክተር ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የዳይሬክተሮች ቦርድ መቋቋም ፣የካውንስል መቋቋም፣ሥልጣን እና ተግባራት

## ፰.የዳይሬክተሮች ቦርድ መቋቋም

፩. በከተማ ደረጃ አሥራ ሁለት አባላት ያሉት ከዚህ በኋላ ‹‹ቦርድ›› እየተባለ የሚጠራ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተቋቁሟል፡፡

፪. ቢሮዉ የቦርዱ ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡

## ፱. የቦርዱ አባላት

፩.ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ.በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የከንቲባዉ የህዝብ ግንኙነት ዋና አማካሪ...............................ሰብሳቢ

ለ.የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ.......ምክትል ሰብሳቢ

ሐ.የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር....................................ፀሐፊ

4. Discharge other related functions designated by the Mayor and the Board.

## 7. Power and Function of the Deputy Director

1. The deputy directors, based on the direction given by the Chief Director, shall:
   a. Assist the chief director in planning, organizing, directing and coordinating the function of the Agency;
   b. Prepare and implement, upon approval, plan of their respective section;
   c. Perform other functions given by the chief director.
2. The deputy director specifically authorized shall perform the functions of the chief director in his absence.

## PART THREE
## ESTABLISHMENT OF BOARD OF DIRECTORS, POWER AND FUNCTIONS AND ESTABLISHMENT OF COUNCIL

## 8. Establishment of the Board of Directors

1. The board of directors consisting of twelve members, hereafter referred to as “Board” is hereby established at City level.
2. The Bureau shall serve as the office of the Board.

## 9. Members of the Board

1. The Board shall have the following members:

a. At the status of Deputy Mayor, the public Relations chief Advisor of the Mayor…………………………………chairperson

b. Head of Trade and Industry Bureau…………………………vice chairperson

c. Director of Micro and Small Scale Enterprise Development Agency ………………Secretary

መ. የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ቢሮ ኃላፊ……………………………………………አባል

ሠ. የከንቲባዉ የህዝብ አደረጃጀት ረዳት አማካሪ………………………………………አባል

ረ. የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኤጀንሲ ዳይሬክተር………………………..አባል

ሰ. የአዲስ ብድርና ቁጠባ አክሲዮን ማህበር ስራ አስኪያጅ……………………………………..አባል

ሸ. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ፕሮጀክት ፅ/ቤት ስራ አስኪያጅ……………………………………..አባል

ቀ. የከተማው ምክትል ስራ አስኪያጅ..................አባል

በ. የምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል ስራ አስኪያጅ....................................................አባል

ተ. በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የወጣቶች ጉዳይ አማካሪ.........................................................አባል

ቸ. በሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ የሴቶች ጉዳይ አማካሪ……………………………………………አባል

፪. በክፍለ ከተማ እና ወረዳ ደረጃ ከቦርዱ ተመሳሳይ ይዘት ያለው እና በቦርዱ የአሰራር መመሪያ ዝርዝሩ እና ኃላፊነቱ የሚዘረዝር የአመራር ስቲሪንግ ኮሚቴ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡

## ፲.የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የኤጀንሲውን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፡-

ሀ. በከፍተኛና በመካከለኛ አመራሩ፣ በግንባር ቀደሙ ኃይል ፣ በሠራተኛው ፣ በአንቀሳቃሾች ፣ በህዝቡ አደረጃቶችና በአጠቃላይም በከተማው ነዋሪ ስለ ዘርፉ የአመለካከት ጥራት እንዲኖር ይሰራል፤

d. Head of Design and Construction Administration Development Bureau…………………...Member

e. Assistant advisor of Public organization to the Mayor…………………………………. Member

f. Director of Technical and Vocational Education and Training Agency…………………...Member

g. Manager of the Addis Credit and Saving Share Company……………………………….Member

h. Manager of the Housing Development and Administration Project Office………… Member

i. Deputy Manager of the City……………Member

j. Manager of Productivity Improvement Center…………………………………..Member

k. Bureau of Youth and Sport Affairs, Advisor of Youth….……………………………….Member

l. Bureau of Women and Children Affairs, Advisor of Women……………………………..Member

2. Steering committee consisting of officials at Sub-city and Wereda level shall be established with similar composition of members to that of the Board. Details of the responsibilities shall be provided by directives to be issued by the Board.

## 10. Power and Function of the Board

The Board shall have the following Powers and Functions:

1. It shall superiorly direct the works of the Agency;
2. Notwithstanding to the general provisions of sub-article 1 of this Article, the Board shall:

a) Work towards existence of attitudinal quality about the sector among the higher and middle level officials, the forefront force, the employee, the operators, the public organizations, and generally residents of the City;

ለ. ልማታዊ የሆኑ አተሳሰቦችና አሰራሮች እንዲጎለብቱ፣የስራ ወዳድነት ባህል እንዲዳብር ሰርቼ ያልፍልኛል የሚል አስተሳሰብ በወጣቱ እና በሌላውም ህብረተሰብ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

ሐ. በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ፣ በአቋራጭ ለመክበር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በአመለካከትም ሆነ በአሠራር እንዲዳከሙ ያደርጋል፤

መ. በአመራሩ፣ በአባላት፣ በሠራተኛው፣ በአንቀሳቃሾች በህዝቡ አደረጃጀቶችና በአጠቃላይ በነዋሪው ውስጥ ሰፊ የክህሎት ችግሮች እንዳሉ በመረዳት ይህንን ክፍተት ለመሙላት ይሠራል፤

ሠ. በዘርፉ የሚታየውን የክህሎት ክፍተት ለመሙላት የተለያዩ ስልጠናዎች መሰጠታቸውን በመከታተል ይቆጣጠራል፡፡ ቴክኖሎጂዎች እንዲዘጋጁ፤ እንዲፈተሹና እንዲሰራጩ ያደርጋል፣ የመሠረታዊ አሠራር ሂደት ለውጡ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣ ፤

ረ. በየጊዜው አደረጃጀቶችንና አሠራሮች እንዲፈተሹ በማድረግ በዘርፉ የአመራር ብቃት ያለመቋረጥ እየተገነባ እየጎለበተ እንዲሄድ በማድረግ ጥራቱን የጠበቀ ምርትና አገልግሎት ከዘርፉ ለገበያ መቅረቡን ያረጋግጣል፣ የህዝቡ ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር በማድረግና ውጤታማ ተግባራት እንዲከናወኑ ይሠራል፤

b) Strengthening of developmental thinking and work procedures, extension of the culture of affection towards job and thereby the idea that the way for change would be working among the youth and other members of the society;

c) Weakening both attitudinally and procedurally, the idea of rent seeking and activities in unlawful enrichment;

d) Understand the problems of skill gap and Work towards the gap among the officials, members, laborers, operators, public organizations and generally the residents;

e) Follow up and supervise different trainings which are offered to fill the skill gap observed in the sector. Prepare technologies; inspect and disseminated; ascertain the Business Process Reengineering is fully implemented;

f) Ascertain quality product and service is supplied to the market from the sector by causing the organization and work procedures timely checked and leading capacity of officials strengthened and built continuously; work towards effective functions by boosting public participation at higher level;

ሰ. የግብአት ችግሮች እንዲቃለሉ ለማድረግ ሰፊ ርብርብ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል:: በዚህም የብድር አገልግሎቱ በሰፊው መቅረቡን፣ የማምረቻና የመሸጫ ሼዶች ወይንም ቦታዎች መዘጋጀታቸውን፣ ለአንቀሳቃሾች የገበያ ትስስር መፈጠሩን፣ የአንቀሳቃሾች ክህሎት ያለማቋረጥ ማደጉን፣ የሥራ ዕድል ተደራጅተው እንዲፈጥሩ መደረጉን፣ በመንግሥት በሚሠሩ ግንባታዎችም ሆነ ሌሎች ሥራዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ መደረጉን፣ ጥሬ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ መደረጉን ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲያገኙ መቻላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል ፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

ሸ. የጥቃቅንና አነስተኛ የልማት ሰራዊት በየጊዜው እየተጠናከረ እየጎለበተ እንዲሄድ ኃላፊነት ወስዶ ይሰራል፡፡

፫. በቦርዱ ውስጥ የተወከሉ የባለድርሻ አካላትን ተግባርና ኃላፊነት ለማሳለጥ የሚያስችል ዝርዝር ተግባር እና የግንኙነት ሁኔታ እንዲሁም በተዋረድ በክፍለ ከተማና በቀበሌ ደረጃ ተግባሮቹ ተዋህደው የሚፈፀሙበትን አግባብ የሚዘረዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፩. ስለ ቦርዱ ስብሰባ

፩. ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤

፪. አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም የቦርድ ስብሳቢው ሰብሰባ መጥራት ይችላል፤

፫. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

g) be responsible to exert effort massively with the view to tackled the problems of input in the sector. To this end, it shall follow up supervise and take appropriate measures regarding that the credit service is widely provided, shades or sites for production and sale are made available, market tie is facilitated for the operators, skill of operators is continuously developed, operators are enabled to get organized and create job opportunities, they are made participate in construction works undertaken by the Government as well as other works, they get raw materials at reasonable cost in their localities and they get one center service;

h) Work with responsibility towards strengthening of the micro and small scale development force from time to time.

3. It may issue directive providing for detailed activities of stakeholders made member of the Board with the view of facilitating their respective functions and responsibilities, conditions of relationship, as well as concerted implementation of the tasks at Sub-city and level.

## 10. Meeting of the Board

1. The Board shall meet at least Once in a Month;
2. In case of emergency, the chairperson may call extraordinary meeting;
3. There shall be a quorum where majority of the members are present;

፬. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባ ላይ ከተገኙ አባላት ከግማሽ በላይ ሲደገፍ ይሆናል፡፡ሆኖም ድምፅ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፪. የበጀት ምንጭ

የኤጀንሲው በጀት ከሚከተሉት ሊገኝ ይችላል፡-

፩. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚመደብ በጀት፡፡

፪. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚደረግ ድጋፍ፡፡

### ፲፫. የሂሣብ መዛግብት አያያዝ

፩. ኤጀንሲው ትክክለኛ የሆኑና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

፪. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብት በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

### ፲፬. ተፈፃሚነት የሌላቸውና የተሻሩ ሕጎች

፩. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፲፬/፪ሺ፩፩ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል፡፡

### ፲፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከጥር ፳ ቀን ፪ሺ፱፪ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፱፪ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

4. Decision of the Board shall be passed by majority members attending the meeting. Where there is a tie, the idea supported by the chairperson shall have a casting vote.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 12. Source of Budget

Budget of the Agency shall be obtained from the following sources:

1. Budget allocated from the Addis Ababa City Government.
2. Aid obtained from the Governmental and Non Governmental organizations.

### 13. Keeping of Book of Accounts

1. The Agency shall keep Accurate and Complete Books of Account.
2. The Book of Accounts of the Agency shall be audited annually by the Chief Auditor of the City Government.

### 14. Inapplicable and Repealed Laws

1. Any Regulation, Directive or Practice inconsistent with this regulation shall have no effect on matters covered in this Regulation.
2. The Addis Ababa City Government Regulation No.14/2009 is hereby repealed fully and Replaced by this Regulation.

### 15. Effective Date

This Regulation shall be effective as of 28th January 2010.

**Addis Ababa**

**28th Day of January, 2010**

**Kuma Demeksa**

**Mayor of Addis Ababa City**